የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
Information Network Security Administration

# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 49/2015

ሰለሞን ሶካ
ዋና ዳይሬክተር

የካቲት 2015 ዓ.ም
ኢ.መደአ

# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
# የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም
# ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 49 /2015

ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ እየጨመረ የመጣዉ የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር በህግ ማስከበርና በብሔራዊ ደህንነት ላይ ስጋት እንዳይደቅን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም አማካኝነት ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ በሀገሪቱ ወጥ፣ ግልፅ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሠራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁ. 808/06 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ (9) እና አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1/ **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቅም ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 49/2015 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2/ **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "አስተዳደር" ማለት ኢንፎሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነው።
2) "ክሪፕቶግራፊክ ምርት" ማለት የምስጠራ ቴክኒኮችን የሚጠቀም ሶፍትዌር ወይም ሃርድ ዌር ሆኖ በመረጃ ላኪዎች ወይም ተቀባዮች መረጃ ወይም የውሂብ ስርዓቶች ደህንነት ትክክለኝነት፣ ምሉዑነት እንዲሁም ትክክለኛ ምንጭ ለማስጠበቅ የሚያገለግል ምርት ወይም አገልግሎት ነው።
3) "የክሪፕቶግራፊክ ምርት ዝውውር" ማለት የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ወደ ሀገር ማስገባት እና ከሀገር ማስወጣት፣ መሸጥ፣ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ እና ማምረትን ያጠቃልላል፤

4) “የክሪፕቶግራፊክ ምርት አጠቃቀም” ማለት የክሪፕቶግራፊክ ምርት ተጠቅሞ አገልግሎቶችን ማግኘት፣ አገልግሎቶችን መስጠት ወይም ተያያዥ ተግባራትን ማከናወን ነው፤

5) “ፍቃድ” ማለት አስተዳደሩ በዚህ ህግ የተቀመጡ ተገቢ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ለሚያዘዋውሩ እና ጥቅም ላይ ለሚያዉሉ አካላት የሚሰጠው ፍቃድ ነው።

6) “ፍተሻ እና ግምገማ” ማለት በደህንነት ስታንዳርዶች መሰረት በክሪፕቶግራፊክ ምርት እና አገልግሎት ላይ የሚደረግ የደህንነት ተጋላጭነት ፍተሻ እና ግምገማ ነው።

7) “ሰው” የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

8) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴት ፆታንም ያካትታል።

3/ <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን በሚያዘዋውሩ እና ጥቅም ላይ በሚያዉሉ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4/ <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም በብሔራዊ ደህንነት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ በመቀነስ፤ ምርቶቹ ለሀገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገት የሚኖራቸውን ፋይዳ የሚያሳድግ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ነው።

## ክፍል ሁለት
## ስለክሪፕቶራፊ ምርቶች ዝውውር እና አጠቃቀም

5/ <u>ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው ተግባራት</u>

1) ማንኛውም ሰው የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ለማዘዋወር ከአስተዳደሩ ተገቢዉን ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

2) ማንኛውም ሰው የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ተጠቅሞ ንግድ፣ ኢንቨስትመንት ወይም መሰል ገቢ የሚያስገኙ ተግባራት ላይ ለመሰማራት በቅድሚያ ከአስተዳደሩ ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ በሀገር ላይ ከሚደቅኑት የደህንነት ስጋት አንፃር ፍቃድ የማይሰጥባቸውን እና ክልከላ የተጣለባቸውን የክሪፕቶግራፊክ ምርት ዓይነቶች ለይቶ ያሳውቃል።

6/ <u>ስለክልከላ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው መሰረት ፍቃድ የሚያስልጋቸውን ተግባራት ላይ ከአስተዳደሩ ፍቃድ ሳይገኙ

የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን በማንኛውም መልኩ ማዘዋውር ወይም ጥቅም ላይ ማዋል የተከለከለ ነው።

2) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ክልከላ የተጣለባቸው የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን በማንኛውም መልኩ ማዘዋወር ወይም ጥቅም ላይ ማዋል የተከለከለ ነው።

3) ማንኛውም ሰው ክርፕቶግራፊክ ምርቶችን በመጠቀም የሚገኙ ምናባዊ ንብረቶችን ወይም ገንዘቦችን በሀገር ውስጥ ለገንዘብ ዝውውርና ገንዘብ ነክ ለሆኑ አገልግሎቶችን ለማግኘትም እንዲሁም ለግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም አይችልም።

## 7/ ስለፍቃድ መስፈርቶች

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገጉትን ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው ተግባራትን ለማከናወን የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት ማቅረብ ይኖርበታል፦

1) የነዋሪነት መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የሕግ ሰውነት ማረጋገጫ ሰነድ፤
2) የክሪፕቶግራፊክ ምርቱ አይነት፣ ቴክኒካል አቅም፣ የምርት ዓመት፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ዓላማ የሚያሳይ ማስረጃ፤
3) የክሪፕቶግራፊ ምርት የተመረተበት ወይም የሚመረትበት ወይም የሚፈጠርበት ወይም አገልግሎቱን የሚሰጥበትን ቋሚ አካላዊ አድራሻዎች (ካርታ ወይም የኪራይ ውል)፤
4) ለክሪፕቶግራፊ አገልግሎትን ወይም ምርትን ለፍቃድ ጠያቂው የሚያቀርብ የሌላ የክሪፕቶግራፊ ምርት ካለ የአቅራቢውን ስም፣ አድራሻ እና ዝርዝር መረጃዎች፤
5) ለውጭ ሀገር አመልካቾችና ኢንቨስትመንት የሚከናወንበት ፕሮፖዛል፤
6) እንደአስፈላጊነቱ እንደሚሰጠው ፈቃድ አይነት ሌሎች አስተዳደሩ የሚያወጣቸው ተጨማሪ ዝርዝር ቴክኒካል መስፈርቶች።

## 8/ የፍቃድ ጥያቄ አቀራረብ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት ፍቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማመልከቻ እና እንደሚፈለገው ፍቃድ አይነት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 የተዘሩዘሩ ቅደመ ሁኔታዎች በአስፈላጊ መረጃዎች በመደገፍ ለአስተዳደሩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በአካል ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል።
2) የሚቀርበው የፍቃድ ጥያቄ በክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ኢንቨስትመንት፣ ንግድ ወይም ማንኛውም ገቢ የሚያስገኝ ተግባር ለመሰማራት ከሆነ ማመልከቻው፤ የፕሮጀክቱን አጭር ማብራሪያ፣ የካፒታሉን መጠን፤ ተግባሩን ለማከናወን የታቀደበት ቦታና ጊዜ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ሊገነባ ያሰበው መሰረተ ልማት መግለፅ ይኖርበታል፡፡

9/ **ዉጤት ስለማወቅ**

1) አስተዳደሩ የቀረበለትን ጥያቄ በ15 /አስራ አምስት/ የስራ ቀናት ዉስጥ በመመርመር ዉጤቱን ለአመልካቹ ያሳዉቃል፤
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 ላይ የተገለፀው እንዳለ ሆኖ አስተዳደሩ የፍቃድ መስጫውን ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ ወይም ውስብስብነት እስከ 1 /አንድ/ ወር ድረስ ሊያራዝም ይችላል፤
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 የተቀመጠውቀ እንደተጠበ ሆኖ አስተዳደሩ አመልካች በተገቢው ጊዜ ፍቃድ መስጠት የማይቻልበትን ምክንያት ለአመልካች እንደአስፈላጊነቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4) አመልካቹ ተገቢውን መስፈርት እና ፍተሻ እና ግምገማዎችን አሟልቶ ሲገኝ ፍቃዱ ይሰጠዋል።
5) የቀረበው ማመልከቻ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም አስፈላጊ ማስረጃዎችን የማያሞላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄዉን ላቀረበዉ አካል በመመሪያዉ መሰረት ያላሟላው መስፈርት ተገልፆ በ1 /አንድ/ ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ይመለስለታል፡፡
6) ፍቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

10/ **ስለፍቃድ ይዘት**

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጥ ፍቃድ ቢያንስ የሚከተሉት ይዘቶች ሊኖሩት ይገባል፦

1) ፍቃድ የተሰጠው ሰው ሙሉ ስም፣ ፎቶ እንዳስፈላጊነቱ እና አድራሻ፤
2) የክሪፕቶግራፊክ ምርቱ ወይም አገልግሎቱን ዝርዝር ሁኔታ፤
3) ፍቃድ የተሰጠበት ዓላማ፤
4) ፍቃድ ሰጪው ስም እና ፊርማ፤ እና
5) ፍቃድ የተሰጠበት እና የሚያበቃበት ቀን፤

11/ **ስለ ፍቃድ እድሳት**

1) ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠው ፍቃድ በየዓመቱ ማሳደስ ይኖርበታል፤
2) ማንኛውም ሰው የተሰጠው ፍቃድ ከማብቃቱ ከሶስት ወር አስቀድሞ የእድሳት ጥያቄ ለአስተዳደሩ ማቅረብ ይኖርበታል፤
3) ማንኛውም ሰው የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲያቀርብ ግብር የከፈለበትን ደረሰኝ ማቅረብ ይኖርበታል፤
4) አስተዳደሩ ፍቃድ እንዲታደስ የተጠየቀው ሰው ተገቢውን መስፈርት እና የኦዲት ፍተሻዎችን አሟልቶ ሲገኝ ፍቃዱን ያድሳል።

12/ <u>ፍቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ</u>

ማንኛውም ፍቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

1) ፍቃዱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ ማንኛውም ተግባር ላይ አለመሰማራት፤
2) የክሪፕቶግራፊክ ምርቱ ለማንኛውም አላማ ከተጠቃሚው ቁጥጥር ውጭ ወይም ስርቆት የደረሰበት እንደሆነ ለአስተዳደሩ ማሳወቅ፤
3) በአስተዳደሩ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን የግዴታ ማስገቢያ ውል የመፈረም፤
4) ማንኛውም የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ላይ ፍቃድ እንዲሰጠው ወይም የተሰጠው ፈቃድ እንዲታደስለት ጠይቆ ተገቢውን መስፈርት ያሟላ ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ በመንግስት በሚወሰነው መሰረት ይፈፅማል፤
5) አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ የፍተሻ እና ግምገማ እንዲሁም የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በማንኛውም ጊዜ ለማድረግ ሲጠይቅ ተገቢውን ትብብር የማድረግ፤
6) ለሚያደረገው ፍተሻ እና ግምገማ እንዲያመች አገልግሎቱን ለመስጠት የሚዘረጋውን ቴክኖሎጂ ስርዓት ለአስተዳደሩ ተደራሽ ያደርጋል /Access privilege/ ፤
7) የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ያስተላለፈላቸውን ወይም ያስታጠቃቸውን አካላት የማሳወቅ፤
8) የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ወይም አገልግሎት ለመስጥ የሚጠቀምባቸውን ቁሶች ለማስወገድ ሲፈልግ ለአስተዳደሩ አስቀድሞ የማሳወቅ፤
9) ምናባዊ ንብረቶች ወይም ገንዘቦችን አስመልክቶ በብሔራዊ ባንክ የሚወጡ ህጎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን የማክበር፤
10) የሚሰጠውን የአገልግሎት አይነት እና ተደራሽነት ሲለውጥ ወይም የሚጠቀምበትን የክሪፕቶግራፊክ ምርት ዓይነት ላይ ለውጥ ሲያደርግ ለአስተዳደሩ የማሳወቅ
11) በኦዲት እና ክትትል ስራዎች ወቅት የሚሰጡትን ማስተካከያዎች የመቀበልና የመተግበር፤
12) ከፍቃዱ ጋር ተያይዞ ያሉ ማንኛውም ለውጦችን የማሳወቅ፤
13) አስተዳደሩ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ያመረታቸውን የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ወይም የሰጣቸውን አገልግሎቶች አስመልክቶ ሪፖርት የማድረግ፤

13/ <u>ፍቃድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ</u>

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ ፍቃድ እንደአግባብነቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰረዝ ይችላል፦

ሀ) ፍቃዱን የወሰደው ሰው በራሱ ፍላጎት ፍቃዱን ሲመልስ

ለ) ፍቃድ የተሰጠው ድርጅት ሲፈርስ፤

ሐ) ፍቃድ ተቀባዩ በህግ ችሎታውን ሲያጣ፤

መ) ፍቃድ የተሰጠበት ምርት ከአላማው ውጭ ወይም ህጋዊ ላልሆነ ዓላማ ሲጠቀም፤

ሰ) ፍቃድ ለማግኘት የቀረበው ማስረጃ ሀሰተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ) በሚደረግ ድንገተኛ ወይም መደበኛ ፍተሻና ግምገማ የፍቃድ መስፈርቶች መጓደላቸው ሲረጋገጥ፤

ሠ) የተሰጠውን ፍቃድ ተጠቅሞ ዜጎችን እና የሀገር ደህንነትን ስጋት የሚፈጥር ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሲገኝ፤

ሸ) በእግድ ላይ እያለ ምርት ሲያመርት ወይም አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከ መ እስከ ሠ የተዘረዘሩት ቢኖሩም፤ አስተዳደሩ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃዱን ከመሰረዙ በፊት ለሁለት ወር ያህል አግዶ ሊያቆይ ይችላል።

14/ <u>ስለፍቃድ እና እድሳት ክፍያዎች</u>

ማንኛውም የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ላይ ፍቃድ እንዲሰጠው ወይም የተሰጠው ፈቃድ እንዲታደስለት ጠይቆ ተገቢውን መስፈርት ያሟላ ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ በመንግስት በሚወሰነው መሰረት ይፈፅማል።

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15/ <u>የቁጥጥር አግባብ</u>

1) አስተዳደሩ ተገቢውን ስርዓት በመዘርጋት አካላዊ እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን ተጠቅሞ የክሪፕቶግራፊክ ምርት ዝውውር ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤
2) አግባብነት ያለው የኦዲት እና ፍተሻ ስራዎችን ይሰራል፤
3) ሪፖርቶችን ለመቀበል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ፍቃድ ከተሰጣቸው ሰዎች በወቅቱ ሪፖርት ይቀበላል፤
4) አስተዳደሩ ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች የመረጃ ቋት በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል፤
5) አስተዳደሩ እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ መሰረት ፍቃድ የሰጣቸውን አካላት ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ የመንግስት አካላት በማሳወቅ ተጨማሪ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው ሊያደርግ ይችላል።

16/ <u>ኦዲት እና ፍተሻ ስለማድረግ</u>

1) አስተዳደሩ የክሪፕቶግራፊክ ምርቶች ዝውውር አጠቃቀም ላይ ፈቃድ ለተሰጣቸው አካላት በየአመቱ ኦዲት እና ፍተሻ ያደርጋል፤

2) አስተዳደሩ እንደ አስፈላጊነቱ ድንገተኛ ፍተሻዎችን ሊያደርግ ይችላል፤

17/ <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛዉም ሰዉ አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ሲወጣ የመተባበር እና ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የሚወስደውን እርምጃ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

18/ <u>ቅጣት</u>

1) ማንኛውም ሰው በአስተዳደሩ የተሰጠ የጸና ፍቃድ ሳይኖረው ወይም ከተሰጠው የፍቃድ አላማ ውጭ በክሪፕቶግራፊ ምርቶች ዝውውር ላይ የተሰማራ እንደሆነ ወይም በማንኛውም መልኩ ምርቶቹን ጥቅም ላይ ካዋለ አግባብነት ባለው ህግ ያለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት በሚወሰነው መሰረት በገንዘብ ይቀጣል፤
2) ማንኛውም ሰው ክልከላ የተደረገበትን የክሪፕቶግራፊክ ምርት ዝውውር ላይ ከተሰማራ ወይም የክሪፕቶግራፊክ ምርቶችን ጥቅም ላይ ካዋለ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል።
3) በዚህ መመሪያ ከተደነገገዉ ዉጪ የፍቃድ አሰጣጡን ስርዓት ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያደናቀፈ ወይም የተላለፈ የአስተዳደሩ ሰራተኛ በዲሲፒሊን እና አግባብ ባለዉ ህግ መሰረት ተጠያቂነት ይሆናል፡፡

19/ <u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1) በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ ማቅረብ ይችላል፤
2) አስተዳደሩ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው መልስ መስጠት ይኖርበታል።

20/ <u>ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

21/ <u>መመሪያ ስለማሻሻል</u>

አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል።

22/ <u>መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጊዜ ጀመሮ ተግባራዊ ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ---- ቀን 2015 ዓ.ም